# ቪኦኤ እንወያይ፥ በየካቲት ወር ውይይት ላይ
# የግል አስተያየት

በዘውገ ፋንታ

*መግብያ*

ብዙ ጊዜ አዲስ ስራ ሲጀመር፣ ሀሳቡን ውይም አቅራቢውን በማኳሸሽና በማጣጣል ሃሳቡ ለቁምነገር ሳይደርስ ቶሎ ይቀጫል። ይህን በመረዳት መልካሙን ውይይት እኔም በነቀፌታ እንዳልጀምረው፣ ይህን ጽሑፍ ለማቅረብ አቅማምቸ ነበር። ዳሩ ግን፣ ከትችት ውጭ ሌላ ሀሳብን የማዳበሪያና ማሻሻያ መንገድ እንደሌለ ተገንዘቤ ይችን ጽሑፍ አዘጋጅቻለሁ። ስለዚህ፣ ውይይቱ እጅግ ጠቃሚ፣ ትችቱም አስፈላጊ ስይጣን መሆኑን መልዕክቴ በማድረግ ይዠ ቀርቤአለሁ። በፍልስፍና ወይም ጠለቅ ባለ ውይይት ላይ ሀሳብን መሰንዘር፣ ዳቦን በሳለ ቢላዎ በወግ መሸርሸር ተገቢ ነው። አለበለዚይ፣ በዶማ እጅ ዳቦውን ቆራርሶ ቅጥ ያጣ የወያኔን ገበታ (አሰተዳደር) እንዳይመስል ተስፋ አረጋለሁ።

የውይይቱ አስተናጋጆቭ ጽዮን እና ሄኖክ ውይይቱን በንቃትና ብልህነት አስተናግደዋል ብዬ አምናለሁ። ትልቅ ምስጋና ይገባቸዋል። አሉላ፣ ጃዋር፣ አቻምየለህና ዶ/ር ደረሰ ያቀረቡት የፖለቲካ ግንዛቤና ትምሕርት ለመረዳት ምርምርን የሚጠይቅ ሆኖ አገኝቸዋለሁ። ስለዚህ፣ ውይይቱ እጅግ ጠቃሚ መሆኑን አስቀድሜ እገልጻለሁ። የኢትዮጵያ ሕብረተስብ በሽግግር ያለ ስለሆነ፣ ካንድ ከቆየ ባህሪ ወደሌላ ለመሸጋገር የረጅም ጊዜ ሙብላላትንና መዳበርን ይጠይቃል። ሆኖም፣ አሁን በከፍተኛ ማዕበል እየተካሄደ ያለው የኢትዮጵያውያን ፖለቲካ፣ ሕዝቡ ይህ ነው በማይባል ጥልቅ ቋንቋ እየተወያየ እንደሆነ መግለጹ ተገቢ ነው። ሀሳቡን የሚገልጽበት አረፍተነገር ከነ ሊቀሊቃውንት የተሻወርቅ ያወደድረዋ ድፍረት አይሆንም ብየ አምናለሁ፤ እንዳይሆንም እጠይቃለሁ። ሊቁ ሆነ ብለውና ሳይሉ የሚናገሯቸውን ቃሎችና ሃሳቦች ለመረዳት ተርጓሚ ያስፈልግ ነበር ይላሉ። የአቶ ተገኝ የተሻወርቅ አባት የሆኑት፣ ሊቀሊቃውንት የተሻወርቅ የወሎና የሐረር ሰው ነበሩ። በቅኔአቸው እጅግ የታወቁ እንደነበሩ ይነገራ። የእያሱ ደጋፊ፣ የአፄ ኃይለሥላሴ ተጻናዋች እንደነበሩም ይታወቃል። የክቡር ይድነቃቸው ተሰማ አባት፣ አለቃ እሸቴ ጋር ጓደኛ እንደነበሩ ተወርቷ።

ሊቀሊቃውንት የተሻወርቅ ዓረፍተ ነገራቸው ሁሉ ጠጠር እንደነበርና በቀላሉ የማይፈታ (የማይተረጎም)ስለነበር፤ የተናገሩት ከንጉሡ ጀሮ ሲደርስ፣ ንጉሡ “አሁን ደግሞ ምን አለ?” ብለዋል ተብሏል።

ማንም ሊቅ ደፍሮ በጥሩም ሆነ በመጥፎ ተርጎሞ ለንጉሡ የሚነግር ሊቅ አልነበረም። ስህተት ብሆንስ! በሚል ፍራቻ። ንጉሡ ብልህም ደግም ነበሩና "በል፣ ያንተን ተወው፣ ልጅህን እናስተምረዋለን" ብለው ተገኘን ወስደው አስተምረው ለትልቅ ደረጃ አደረሱት ይባላል። ይህን ታሪክ  ጎልጉየ ያለቦታው ከዚህ የጠቀስኩበት ምክንያት፣ ጽዮንና ዶ/ር ደረሰ የፌስቡክን ታዳሚ በቋንቋ አጠቃቀማቸው ዘለብ እንዲሉና ጭምትነት እንዲያሳዩ ሲማለዱ ሰምቸ ነው። እኔ ደግሞ በፌስቡክ የሚካሄደውን የፖለቲካ ምልልስና እንካስላንቴ፣ ቋንቋችሁ ጠጥሯልና እባካችሁ አቅሉት ማለት ይሻላል ብዬ ለመጠቆም፣ የሊቀሊቃውንት ተሻወርቅን ታሪክ ምሳሌ አድርጌ አቀረብኩ። በዲሞክራሲ ገና ሳንድህ፣ ስለ ሙብት በአማርኛ ቋንቋ እንደሚገለጸው ከሆነ፣ አሜሪካንን ሳናስንቅ አንቀርም ባይ ነኝ። እኒህ እንግዶች የሚጠቀሙበትን አማረኛ ከሰማችሁ ትስማማላችሁ።

የወያኔ አዋጅ

በገደል አፋፍ ላይ ያለው ብረት ታጣቂው ወራሪ ወያኔ፣ ለፍጻሜው የቀረውን አስፈላጊ እርምጃ በአዋጅ አራዝሟል። በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፊ ውይይት ተደርጓል። ከተወያዮቹ አንዳቸውም አዋጁን አልደገፉም። አንዳዶቹ በአንዳንድ ትግሪዎች ንብረት ላይ የተፈጸመው እንዳይቀጥል የተወሰደ አስፈላጊ ርምጃ መሆኑን ለመግለጽ ሞክረዋል። ሌሎቹ ወያኔ በመላው ኢትዮጵያ ክፍለግዛቶች  በሕዝብ ላይ የፈጸመው የግፍ ጭፍጨፋ ከዚህ ደረጃ እንዳደረሰው አመልክተዋል። ሕዝብ የወሰደው አጸፌታ ሳይሆን፣ የሱ በደል እንዲቆምና የሚሻውን መንግሥት እንዲያቋቁም ሙብቱን ለማስከበር እንደሆነ ጃዋርና አቻምየለህ ገልጸዋ።

ዶ/ር ደረሰም የሕዝብን መንፈስ በምሳሌ እያረጉ አስረድተዋል። ማናቸውም የትግራይ ሰው በተራው መዘረፍና መባረር ይገባዋል አላሉም። ያሳዩት  አርቆ አስተሳሰብና ህሊና እጅግ የሚደነቅ ነው። የትግራይ ሕዝብ በሁለት ቢላዎ የሚበላ መስሎ ቢታይም፣ በመካከላቸው ደግሞ፣ ለመላው ኢትዮጵያ ወገኑ የሞተና የሚታገለ እንዳለ አስረድተዋል። ከኑግ ጋር የተገኘሽ ሰሊጥ የሚሉት እንዳይሆን፣ የሀገርን አሳሳቢ ጉዳይ እነዚህ የተከበሩ ሰዎች እንደ ወያኔ ልብና ምግባር ሳይሆን፣ እንደ ኢትዮጵያዊነት ያላቸውን ኃላፊነት፣ ለዘላቂ ሰላም በማሰብ ጉዳት በማንም ሰው ላይ እንዳይፈጸም የጸና ሀሳባቸው አስተጋብተዋል።

አሉላ ስለ አዋጁና ዘራፊ ስላለው ሕዝብ

አሉላ ዘረፋን ለማቆምና ጸጥታን ለማስከበር አዋጁ ጠቃሚ ነው ብሏል። ይህ እጅግ ለህሊና የሚዘገንን አጸያፊ ሀሳብ ሆኖ አገኘቸዋለሁ። የወያኔ ድርጊት ያስከተለው የራሱ መጥፊያ ስለሆነ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግ በዘረፋ አስመስሎ ለማስቆም የታቀደ አዋጁ ስለሆነ ተወግዟል። ዳሩ ግን አሉላ፣ የሕዝቡን የነጻነት ትግል እንደ ዘረፋ መቁጠሩ ህሊናቢስነት ሆኗል ብል ስህተት አይመስለኝም። በዚህ ጉዳይ ማንንም ይሉኝታ አያግደውም። አሉላ አዋጁ ዘረፋውን ለማገድ ነው ሲል ያቀረበው ሀሳብ በዕርግጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በትግራዮች ላይ ያነጻጸረ አድርጎ ማየቱና ለማሳየት መሞከሩ ነው። ጥልቅ ዕውቀት የሌላቸው ከማይገባቸው ቦታ ሲገኙ ትልቅ ቀውስ ይፈጥራሉ። ይህ አንዱ ነው። የተጎዳን ሕዝብ ማስተባበያ ቃል አይደለም። እንኳን አንድ ሰው፣ የኢትዮጵያ ኃብት በየደቂቃው የሚዘረፈውን

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያየውና የሚገነዘበው ነው። ለዚያ ዘርፉ ነው አዋጅ የሚያስፈልግ። ጃዋርና ደረሰ በይሉኝታ ሳይሆን በላቀ አስተሳሰብና ህሊና፣ ስለ ዘላቂ ሰላም ጥሩ ሀሳብ ቢያስተጋቡም፣ የኢትዮጵያ ሕዝብን እንቅስቃሴ የሚያግድ አይሆንም። አሉላ ማወቅ የሚገባው፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘራፊም በለው ጸረሰላም 'የራስህ ጉዳይ' ሊለው እንደሚችል ነው። ወያኔዎች እንደነ አባይ ጸሐይና መስፍን ስዩም ሌሎቹም ሲያልሙት የሰነበቱት የዕልቂት ድርጊት እራሳቸው እንደጀመሩት ሊፈጸም እንደሚችል ወለንፋው የማይሰማው ሰው መናጢውና ዋናው ጎጠኛ ሚቹ መለስ ዘናዊና ብቻ ነው። ለወያኔ አስተሳሰብ ባሪያ የሆነ ሰው የወያኔን አጭር ዕድሜ የሚጎናጸፍ ይሆናል። ለውጥ የባሰ ዘረፋና ጭፍጨፋ እንደሚያስከትል ተገንዝቦ፣ መልካሙን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከማስቆጣት መቆጠብ ይኖርበታል። ሌባና ጆሮ ጠቢ ሆኖ ወገንን ሲያስገድል የቆየው፣ ለሚደርስበት አጸፌታ መጨነቅና መመጻደቅ ማንንም አያባባም። ይህ ደግሞ፣ በአንድ ዘርፍ ሕዝብ ያተኮረ ሳይሆን በሁሉም ዘርፎች ውስጥ ያሉትን ከሀዲዎች የሚመለከት ነው።

ስለ አዲሱ ጠቅላይ ምንስትር

ሌላው ውይይት አዲሱን ጠ/ም አስመልክቶ ነበር። በዚህ ላይ ጎልቶ የታየው አስተሳሰብ፣ ኃይለማርያምን 'እከሌ' ቢተካው 'ሌላ አሻንጉሊት' በማለት ነገሩን አጣጥለውታል። የሁልም ሀሳብ በዚህ አመለካከት ላይ ያዘነበለ ይመስላል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ታጥቆ የተነሳበትን ጉዳይ ወያኔ ስቶ 'ማንን ሰው ይፈልጋሉ?' 'እኛስ ማንን እንፈልጋለን?' በሚል ከንቱ ሀሳብ ውስጥ እንደሚዋዥቁ የተወረወሩት ሃሳቦች አመልክተዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄውን እያሰፋ፣ ሃሳቡንም እየለወጠ ነው። ወያኔም እየተቦረቦረ እጁን እየሰጠ መሄዱ ግልጽ ሆኗል። የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገውን ድል ለመቀናጀት ከግቡ አጠገብ ነው። አዋጁ እንደተባለው ሕዝብን ከባለጌ ዘራፊ ስራ ለማቆም ሳይሆን፣ ወያኔ በሰላም የሚወርድበትን ሁኔታ እየፈለገ ነው ብሎ ማሰቡ ትክክል ይሆናል። ማንም ዱር እንዲመለስ አይሻም። ሌላ ቀውስም እንዲመጣ አይፈለግም። ለምሳሌ ኤርትራ ጅብ ሞተ ብላ ጣልቃ እንዳትገባ ብዙ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል። የዱር ጓደኞቹን ፈልጎ ሕጻናትንና ንጹሑን ሰው እንዳይጨርስ ለዚህ መጋለጥ አያስፈልግም። ለውጥ በቀላሉ አይፈጸምም። ይህን አስመልክቶ የሽግግር መንግሥት እንዴት እንደሚቋቋም የተለያዩ እቅዶችን እኔም በበኩሌ ደጋግሜ አቅርቤአለሁ። ወያኔ ከሚዘርፍበት ስነስርዓት የሚያቆመውን ሀሳብ አይወድም። አያነብም ማንበብም አይችል። ግን፣ በመደናበር ከላይ-ታች እያሉ መሆናቸው ይገመታል። ወዳጅ (ጌታ) የሚሉት ሁሉ አሁን እየራቃቸው ነው። ሌሎችም እጃቸውን ከሚመጣው ጥፋት ንጹህ ለማድረግ  እየራቁ መሆናቸው ግልጽ ነው። ወያኔ ያለነሱ መላና ምክር የሚያደርጉትን አያውቁም። ይህ ከባድ የሀገር ጉዳይ ነው። የኢትዮጵያ አስተዳደር፣ በጠጅ ቤት አዘውታሪዎች እጅ ስለገባ፣ ግፍተኞች የሚመሯት ሀገር ትመስላለች። አለን፣ አለን ባዮቹ አሁን አማላጅ ሆነዋል። አለመተማመን ሰፍኗል። የዛሬው ውሳኔ ነገ በሌላው ግለፍተኛ እየተገለበጠ፣ በመደፋፈርና በመናናቅ እልህ ውስጥ እንዳሉና አንድ ምሽት እንዳይጨራረሱ እጅግ በጣም ትልቅ ፍርቻ አለ። ይህ የማይቀር ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ካለበት ሁኔታ ወጥቶ በነሱ የሚነሳውን ዕልቂት ለማብረድና ሰላም ጠባቂና ህግ አስከባሪ ሆኖ የሚታይበት ጊዜ ረጅም አይደለ።

አሉላ ስለ ወያኔ አስተዳደር

አሉላ ስርዓቱ መልካም ነው፡ ሰወቹ (ባለሥልጣኖቹ) መቀየር አለባቸው የሚል ሀሳብ ጠቅሷል። ወያኔዎች ለቀው ከወጡ እውነተኛው ሌብነት፣ ዝርፊያና ግድያ ቆመ ማለት ይሆናል። በአንድ ጎሳ የተወረረው ስልጣንና መስሪያ ቤት ይስተካከላል። ይህ ለውይይት የሚቀርብ ጉዳይ ባይሆንም አሉላ ይቀበለዋል የሚል ግምት አለኝ። ግን ምርጫ አይኖርም። ኢትዮጵያኖች የትም ግዛት የመኖር መብታቸው እንደሆነ ሁሉም ተስማምተዋል። ዳሩ ግን፣ ይህ መብት ከፌደራል አመሰራረት ጋር የተጣመረ እንደሆነና ያንንም መሻር እንደሚያስፈልግ አልተወያይበትም። የጊዜውን የፌደራል አወቃቀር አሉላና ጃዋር የተቀበሉት ይመስላል። “እኔ ካንተ ጋር በዚህ አልስማማም፣ በዚያ ላይ እስማማለሁ” የሚል ሀሳብ እየተረጨ ነበር። የጎሳና የዘርፎች ጉዳይ የሚደፈር አርዕስት አይደለም። የኢትዮጵያ አዲሱ ፌደራል ሲመሰረት፣ መብቶች በጎሳ ወይስ በግለሰብ የሚለው ጥያቄ፣ ብዙ ምሑራኖች የሚንጓለሉበት መስፈሪያ ይሆናል። ስለዚህ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕገመንግሥት በጎሳ ወይም በግለሰብ መብት ላይ ይመስረት የሚለው ጥያቄ ሰፊ የውይይት መድረክ አላገኘም። የምሑራን አንዱ ችግር፣ እንደ ተራው ሰው፣ በምንስማማው እንቀጥል፣ በማንስማማው ልዩነታችንን ተቀብለን ተስማምተን ጠላችንን ፉት እያልን እንኑር የሚለው ሀሳብ ነው። ማንም ሰው ከሌላው ጋር ተወያይቶ አንድን ችግር ሊፈታ ካልቻለ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ እስከ መጨረሻው ዶልቶ ውሳኔ ይሰጥበታል። ስለዚህ፣ የሁለት ሰዎች መስማማት ወይም አለመስማማት እምንት ነገር ናት። ጃዋርና አሉላ ለጤና ያርግላቸውና ሲስማሙ አምሽተዋል። ጃዋር መቀለድ ይችልበታል፤ በዚህ ከቀጠለና የግለሰብን መብትን ከጎሳ መብት አብልጦ ካየና የዚህ ፍልስፍና አራማጅ ከሆነ፣ የፖለቲካው አድማስ መላው ኢትዮጵያ ይሆናል።

የአማራውና ኦሮሞው የተፈጥሮ ውኽደትኦሮሞና አማራው ጥንት ጀምሮ ሲዋኸድ የኖረው የተፈጥሮ ሂደትን ተከትሎ ነው። ክወንዝ ወዲህ ሳዱላ ሲጠፉ፣ ከወንዝ ማዶ ይፈለጋል። መንደር ሰፋ ማለት ነው። ወራሪ ሲመጣ ዘማች ይሄዳል። ጠላት አባሮ የመንደር ልጅ አግብቶ ከዚያው ይቀመጣል። ሌላ ደግሞ፣ ሀገርን የማቅናት ሂደት አለ። የኦሮሞው የማቅናት ማዕበል ያሁኒቱን ኢትዮጵያ ፈጥሯል። ውኽደቱ ሰፊ ነው። ሥልጣኔ ውኽደቱን እጅግ አፋፍሞታል። ሰውም፣ ተፈጥሮም አግዘዋል። የሁለቱ ጎሳዎች መዋኸድ የፖለቲካ ሚና ያለበት ቢመስልም፣ አብዝኸኛው ውኽደት ያለዕቅድ የሆነ ነው። ወያኔ አጥብቆ የታገለው ይኸንን የዘመናት መዋኸድን ለመበተንና ለማጥፋት ነበር። ወያኔ የኢትዮጵያ ወገንና ዜጎች የነበሩትን በከፍተኛ ሴራ አባረረ። ያሁኒቷ ኢትዮጵያ የረጅም ልማትና ዕድገት ውጤት ናት። አንዳንድ ሰዎች ይህን የሕዝብንና የሀገርን ስፋት እንደ ዕድገት አይወስዱት ይሆናል። ወይም ሌላ ትርጉም ሊፈጥሩለት ይሞክሩ ይሆናል። አሁን ያለንበት ወቅት፣ ኢትዮጵያ የምትበለጽገውና ዕድገት የሚመጣው በነዚህ በሁለቱና በሌሎቹ ዕንቁ ጎሳዎች ጉልበትና ጥበብ አማካይነት ነው። ትምህርት ከተፈለገ፣ ኢትዮጵያ ለኤርትርያ ምን እንደሆነች ከማንም ሰው ይበልጥ በረከት ኃብተስላሴ የሚናገረው ያምራል። አንድ ጊዜ የከዳት እናቱን ኢትዮጵያን ሲያወድስ፣ ‘ኤርትሪያ ያለ ኢትዮጵያ’እኔ እንደተሰማኝ ዛፍ ያለውሃ እንደማያድግ አድርጎ ገልጾታል። ኤርትራ አድጋ በቅቷቷል። ኢትዮጵያ በዓለም እጅግ አስናቂ የሆነ የፌደራል አወቃቀር ታወጣለች።

አወናባጁ የብሄርና ብሄረሰቦች መንፈስ

ብሔር እና ብሄረሰብ የሚባሉት ቃልች አሁንም በፖለቲካ አስተሳሰብ እያወናበዱን ነው። ብሔር የግዕዝ ቃል ነው። ብሔር ሲባል፣ ያንድ ወገንና ዜጋ ሀገር የሆነ ማለት ነው። ብሔረሰብ ደግሞ ያንድ ሀገር ሕዝብ ወይም ወገን ማለት ነው። በእንግሊዝኛ "ናሽናል" (National)ማለት ነው። "ናሺናሊቲ" (Nationality) ወገን ማለት ነው። ብሔረሰብ ነጠላም ብዙም ነው። ያንድ ሀገር ሕዝብ እንጂ የአንድ ሀገር ሕዝቦች አይባልም። ለምሳሌ የአሜሪካ ሕዝብ እንጂ የአሜሪካ ሕዝቦች አይባልም። (American people) እንጂ (American peoples) አይባልም። ይህ ደግሞ፣ የኢትዮጵያ ህዝቦች ማለት ስህተት መሆኑን ያስረዳል። ብሔረሰቦች ከግዕዝ የተራባ የአማርኛ ቃል ነው። ስለዚህ፣ ትክክሉ ቃል ብሔረሰብ ነው። ብዙውን ነጠላ፣ ነጠላውን ብዙ የሚያደርግ ቃል ነው። በዚህ አንጻር፣ ብሔር ብሔረሰብ ትክክል አባባል ሲሆን፣ ብሔር ብሔረሰቦች ማለት ትርጉሙ ሌላ ነው። ኢትዮጵያ አንድ ወገን ብቻ ነው ያላት። ይህ በዐለም ዕውቅና ያለው ነው። በዚህ ዕውቅ ሕግ ከሄድን ወገንነት አይቀየርም ወይም አይለወጥም። ዜግነት ግን ሊለዋወጥ ይችላል። ለምሳሌ ኤርትርያኖች የኢትዮጵያ ወገን ናቸው። በዚግነታቸው ኤርትርያ ናቸው። ኢትዮጵያኖች የአሜሪካዊ ዜጎች ቢሆኑ፣ ወገንነታቸው ግን፣ ኢትዮጵያዊ ነው።

በዚህ ጉዳይ ብዙ ለማለት ያበቃኝ፣ በውይይቱ ላይ፣ "የኢትዮጵያ ዜጋ የሚባል ነገር አለ እንዴ?" ሲል አንዱ ሌላውን ሲጠይቅ ስለሰማሁ ነው። በተፈጥሮ ማናቸውም የኢትዮጵያ ወገን፣ የኢትዮጵያ ዜጋ ነው። እራሱ ምሎና ተገዝቶ ዜግነቱን እስከ አልቀየረ ድረስ፣ የኢትዮጵያ ዜግነቱን ማንም የማይቀማው መብቱ ነው። ኢትዮጵያ ለአንዱ አረብ ዜግነትን ሰጥታ ልትቀማ ትችላለች። ወያኔ ትርግራይ የሚባል ቅኝ ግዛት ፈጥሮ፣ ገንጥሎና ተገንጥሎ ለመኖር ያቀደው የጥፋት ዕቅድ ተጸንስሶ እንዳለ ነው።

በ 1960 ቹ በዩኒቨርሲት ተማሪዎች አስተሳሰብ 'ጎሰኛ' የሚለው ቃል ከሀገር ይልቅ ለጎሳ ተቆርቋሪ መሆኑን የሚያሳይ ቁንጭል አስተሳሰብ ሆኖ ስለታየ አስጸያፊ ቃል ሆኖ ተወሰደ። ይህን ሀሳብ መለስ ዜናዊ ተጠቅሞ፣ የጎራ አስተሳሰብ ያጠቃቸውን ጓደኞቹን እነ ሰዬ አብርሃምን "ጎጠኞች" ብሎ ሰደባቸው። ስለዚህ በሀገር ውስጥ ያሉትን ዘርፎችና ጎሳዎች ብሔር-ብሔረሰብ ማለት ተጀመረ። የዚህንም ቃል በኢትዮጵያ ፖለቲካ አጠቃቀም ያስገባው ዋለልኝ መኮንን ሆኖ ሲታወቅ፣ በጥናትና በምርምር ረገድ የሆነ አልነበረም። የፖለቲካ ቃል ሆነ። ብሄር ብሄረስብ ምንም እንከን የማይገኝበት የግዕዝ ቃል ሲሆን፣ ሀገርና ወገን ማለት ነው። ችግር ያስከተለው 'ብሔር ብሔረሰቦች' የሚለው ቃል ሆኗል። ይኼም ብዙ የተለያዩ ሕዝቦች በአንድ ሀገር ውስጥ ያሉ ስላስመሰለው ነው። ይህ ስህተት ሌላ ጥፋት አስተሳሰብ አፍልቋል። መከፋፈልና መገንጠል የሚችሉ እንደሆኑ ታላቁ ሰይጣን መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያ ሕገመንግሥት ህልውና እንዲሆን አደረገ። ለዚሁ መገነጣጠል ሲል የሀገሪቱን ምድር ለብጥብጥ አመቻችቶ ፌደሬሽን መሰረተ። ጃዋር፣ አሉላና ሄኖክ የሚስማሙበት የፌደራል ሲስትም እንደሆነ ጠቁሟል። ዶ/ር ገሰሰ በዚህ ላይ እጅግ የላቀ የኢትዮጵያውያንን ፍልስፍና አሳምሮ አቅርቦታል።

ትዝብት

በሄኖክና በአቻምየለህ መካከል የቆየ የሀሳብ ግጭት እንደነበረ የተሰማኝን ትዝብት ለመጥቀስ እሻለሁ። በተለይ አስተናጋጁ በአቻምየለህ ላይ ተጽዕኖ ለማድረግ የሞከረ መስሎ ስለታየኝ የነበረውን ኃላፊነት የዘነጋ መሰሎኛል። የያዘውን ኃላፊነት እየሳተ ደጋግሞ ያሳየው ባህሪ አስፈላጊ እንዳልሆነ በትህትና እገልጻለሁ። አቻምየለህ ከአፉ ያልወጣውን ብለሀል ብሎ ጠምዝዞ ያቀረበው እጅግ ጣዕመቢስ ቅጽበት ሆኖ አገኝቸዋለሁ። በአሉላና በጃዋር መካከል የነበረው መግባባትና ስምምነት ያስንቃል። ጃዋርን ጠልቄ አላውቀውም፣ ግን አንድ ቪድዮ ተመልክቸ አሚሪካ ያለና አሜሪካ ዩኒቨርስቲ ገብቶ የተማረ አልመሰለኝም ነበር። ማንም የፖለቲካ ሰው አጀማመሩ እጅግ ጠባብና ጎጠኛ ያስመስለዋል። ጃዋር መድረክ ሲገባ (ብዙ ፊት መቶታል) ሕዝብ ጠራርቦና አስተካክሎ ከጎሳ የሀገር መሪ እንዲሆን ያበቃዋል። ጃዋር በኢትዮጵያ ቅርጽ እየታነጸ ነው። ትልቅ ለውጥ አይቸበታለሁ። የኢትዮጵያ መሪ ለመሆን ትንሽ እየፋቀ የሚጥላቸው አንዳንድ የፖለቲካ እንከኖች አሉ። ከእሱ አንዱ፣ ኢትዮጵያ በጅምላ መብት ወይስ በግለሰብ (በተናጠል) መብት ላይ ትመሰረት? የሚለውን ጥያቄ አስመልክቶ ነው።

መደምደሚያ

ጽዮን መልካም ውይይት እንዲሆን በሚያስችላት ዕውቀትና ባሕሪ በብቃት አስተናድጋለች። አክብሮቴን እገልጻለሁ። የተዛባውን የውይይት መድረክ በሚገባ አካሂዳለች። ሄኖክ የአድማጭን መንፈስ መከታተል አለበት። ትንሽ ስህተቱ እጅግ ጎልታ ትታያለች። አንድ ጊዜ አድማጭ እንከን ካየና ከተገነዘበ፣ ሁልጊዜ የምታረገው ይመስላዋል። ስለዚህ፣ 'ክላ' የሚለው ሲበዛ የምትወደው ስራ እንድትጠላ ያረጋል። መሆን የለበትም። ከእንግዶች ጋር ልዩነት ይኖራል። ግን ትንሽ የተዛባች አስተያየት ካየ፣ አድማጭና ተመልካች፣ ሆድ የባሰው ስለሆነ ዘለፋውን ያንጋጋብሀል። ይህን ችግር መላ በለው እላለሁ።

የድካማችሁ እንዲያፈራና ስራችሁ ጥራት እንዲኖረው ይህን አስተያየት በትህትና አቅርቤአለሁ። በመጨረሻ ሁለታችሁም ለኢትዮጵያ ለውጥ ሰፊ አስተዋጽዖ የምታደርጉ ናችሁ ብዬ አምናለሁ። ይህም ደግሞ ከልቤ የመነጨ አስተያየት ነው።

በዚህ ጽሑፍ ላይ አስተያየት ካለዎት ጸሐፊውን ለማገኘት፥

zegfanta@outlook.com

voa

https://www.youtube.com/watch?v=odgLdPqwFl8